**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**

# ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

## ትኩረት የሚሹ በሽታዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

**ማውጫ** ........ i

1. መግቢያ ........ 1

2. ዓላማ ........ 1

2.1. አጠቃላይ አላማ ........ 1

2.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 1

3. በደረጃ ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበራቸው. 2

3.1. መሰረታዊ መረጃን ማሰባሰብና መተንተን ........ 2

3.2. የማህበረሰብ ንቅናቄን መፍጠር ........ 2

3.3. የማሕበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ለሚስፈልጋቸው ትሮፒካል በሽታዎች ቅደመ መድኃኒት ስርጭት ዝግጅት ማድረግ ........ 3

3.4. ትራኮማ (የአይን ማዝ) መከላከልና ማጥፋት ........ 4

3.5. የኦንኮሰርኪያሲስ እና ተላላፊ የሆነው የዝሆኔ በሽታ መከላከልና ማጥፋት ........ 6

3.5.1. ኦንኮሰርኪያስስን መከላከል መቆጣጠር ........ 6

3.5.2. ተላላፊ የሆነው ዝሆኔን መከላከልና መቆጣጠር ........ 7

3.6. ተላላፊ ያልሆነው ዝሆኔ (ፖዶኮኒዮሲስ) መከላከልና ቁጥጥር ........ 10

3.7. የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች እና ለቢልሃርዚያ (ሽስቶሶሚያሲስ) በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ........ 12

3.7.1. የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መከላከል እና መቆጣጠር ........ 12

3.7.2. ለቢልሃርዚያ (ሽስቶሶሚያሲስ) በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር ........ 14

3.8. ሊሽማኒያሲስ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ........ 18

3.9. ጊኒዎርም በሽታ (ድራኩንኩልያሲስ) ጨርሶ ማጥፋት ........ 19

3.10. ድህረ ማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ........ 20

3.11. የቬክተር ቁጥጥር ማድረግ ........ 20

4. አግልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ........ 22

5. የደረጃ አራት ጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከደረጃ 3 ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር እንዴት ተባብረው ይሰራሉ? ..... **Error! Bookmark not defined.**

6. ጤና ኬላ ጤና ጣቢያ ትስስር ..... 23

7. የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 23

8. ክትትልና ግምገማ ..... 23

8.1. ክትትል ..... 23

8.2. ግምገማ ..... 24

8.3. ትኩረት የሚሹ በሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር ግምገማ መለኪያዎች ..... 24

9. ቅጥያ ..... **Error! Bookmark not defined.**

## 1. መግቢያ

ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች በአብዛኛው ተላላፊ ሲሆኑ በዐይን በማይታዩ በሽታን በሚያስተላልፉ ረቂቅ ተህዋስያን አማካይነት ከታመመው ሰው ወደ ጤናማ ሰው በተለያዩ መንገዶች በመተላለፍ ህመምን በማስከተል አልፎም ሰፊ የህብረተሰብ ክፍልን ለአካል ጉዳትና ለሞት የሚዳርጉ በሽታዎች ናቸው፡፡

በሀገራችንም በህብረተሰብ ላይ ከፍተኛ የጤና ችግር በማድረስ ጎልተው ከሚታወቁት ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች መካከል ትራኮማ (የዓይን ማዝ)፣ ኦንኮሰርኪያሲስ /ፎከት/ ፣ተላላፊና የማይተላፍ ዝሆኔ፣ ቢሊሀርዚያ /የደም ወስፋት/፣ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች፣ሊምፋቲክ ፊላሪያሲስ፣ ሌሽማኒያሲስ (ካላዛር/ቁንጭር) ፣ድራንኩሊያሲስ (ጊኒዎርም) ናቸው፡፡

እነኚህ በሽታዎች በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ችግር ሲሆኑ ካላቸው ስርጭትና እያደረሱት ካለው ጉዳት ባሻገር በሽታዎቹን መቆጣጠርና የህብረተሰብ ጤና ችግር መሆናቸው እንዲያከትም ከማድረግ አንጻር በተበጣጠሰና በዘመቻ መልኩ ቢሆኑም በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎች ተጠናክረው ተፈጻሚ እንዲሆኑ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል:: ስለዚህ ትከረት የሚሹ በሽታዎች ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠርና አገልግሎቱን የበለጠ ለማጠናከርና በሁሉም አካባቢዎች ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ ጋር በመደበኛነት በማቀናጀት በስፋት ለማዳረስ እንዲቻል ይህ የሁለተኛ ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ፓኬጅ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በዓለም ጤና ድርጅት የተለዩት ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች በርካታ ቢሆኑም በዚህ ሁለተኛ ትውልድ የተካተቱት በሀገራችን በስፋት የሚታዩ ስምንት በሽታዎች ሲሆኑ እነዚህም ትራኮማ (የዓይን ማዝ)፣ ኦንኮሰርኪያሲስ /ፎከት/ ፣ ተላላፊ ዝሆኔ (ሊምፋቲክ ፊላሪያሲስ)፣ የማይተላፍ ዝሆኔ (ፖዶኮኖሲስ)፣ ቢሊሀርዚያ /የደም ወስፋት/፣ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች፣ ፣ሌሽማኒያሲስ (ካላዛር/ቁንጭር) ፣ድራንኩሊያሲስ (ጊኒዎርም) ናቸው፡፡

## 2. ዓላማ

### 2.1. አጠቃላይ አላማ

ህብረተሰቡን ያሳተፈ ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች በመከላከልና በመቆጣጠር በእነዚህ በሽታዎች የሚከሰተውን ህመም፣ የአካል ጉዳት እና ሞት ማስቀረት ብሎም የህብረተሰብ ጤና ችግር ወደማይደርስበት ደረጃ ማድረስ፣

### 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ህብረተሰቡ ትኩረት በሚሹ የትሮፒካል በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ላይ ያለውን እውቀት እና ክህሎት ማዳበር

- የማህበረሰብ አቀፍ የመድኃኒት ስርጭት ለሚያስፈልጋቸው ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አቅርቦት ማሻሻል፣
- ሕክምና ለሚፈልጉ ህሙማን አስፈላጊውን ሕክምና በመስጠት ሊከሰት የሚችለውን ህመም መቀነስ እና የአካል ጉዳት እንዳይከሰት መከላከል
- በበሽታዎቹ መዘዝ ሊመጣ የሚችለውን ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ጫናን መቀነስ

# 3. በጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትና አተገባበራቸው

## 3.1. መሰረታዊ መረጃን ማሰባሰብና መተንተን

- ለመድኃኒት ስርጭት የሚያገለግል በየዓመቱ የቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር ወቅታዊ ማድረግ (update)። ይህም ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ወይም የቤተሰብ ማህደርን (Family Folder) በማጣቀስ የሚሰራ ይሆናል።
- ፊት መታጠብ፣ የመጸዳጃ ቤት አጠቃቀም እና ስለአጠቃላይ የግል እና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ላይ በቀበሌ ደረጃ ዳሰሳ ማከናወን እና የመፍትሄ አቅጣጫ መጠቆም
- የአፍለኛ ትራኮማ ስርጭት በትምህርት ቤት ደረጃ መለየትና ለተጨማሪ ምርመራና ህክምና ከጤና ጣቢያ ጋር ማስተሳሰር
- የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች መመዝገብ እና አገልግሎቱ ወደሚሰጥበት የጤና ተቋም መላክ
- በቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታ ታማሚዎች እና ተጠርጣሪ ሰዎች መለየትና ምዝገባ ማካሄድ ።
- ለአንጀት ጥገኛ ትላትሎችና ለሽስቶሶሚያሲስ በሽታ ቁጥጥር (STH control) የሚያገለግሉ አካባቢያዊ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ማጠናከር እና መተንተን
- በአካባቢው የሚገኙ የውሃ አካላት፣ ህብረተሰቡ ለመጠጥ፣ ለምግብ ዝግጅት፣ ለንጽህና፣ እና ሌሎች የቤት ውሰጥ አገልግሎት የሚጠቀምባቸውን የውሃ ቦታዎች መለየት
- የጊኒዎርምን በሽታ ከሀገራችን ለማጥፋት የሚያስችል መረጃዎችን ማጠናቀር።

## 3.2. የማህበረሰብ ግንዛቤን መፍጠር

- በቀበሌ ደረጃ የሚካሄዱቱን ሕዝባዊ ስብሰባዎችና መድረኮች በመጠቀም ትኩረት ስለሚሹ ትሮፒካል በሽታዎች አስከፊነትና ችግሩ ምን ያህል በማህበረሰቡ ውስጥ የተንሰራፈ መሆኑን በማስጨበጥ ለችግሩ የጋራ መፍትሄና ርብርብ እንዲደረግ ማድረግ

- የልማት ቡድን፣ የሴቶች፣ የወጣቶች ማህበራት፣ የቀበሌ አመራር፣ የሀይማኖት ተቋማት እና ትምህርት ቤቶችን በመጠቀም የማህበረሰቡን ግንዛቤ ትኩረት ስለሚሹ ትሮፒካል በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር ላይ በቀጣይነት ማዳበር
- የማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት እደላ ከመካሄዱ በፊት የቀበሌው ካቢኔ አባላት፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሐይማኖት መሪዎች በተገኙበት በጉዳዩ ላይ ውይይት ማድረግ
- በዘመቻ የዓይን ቆብ ቀዶ ህክምና በሚሰጥበት ወቀት ችግሩ ያለበት ሰው ወደ አገልግሎት መስጫ ስፈራ እንዲሄድ ህብረተሰቡን መቀስቀስ
- ወላጆች ዕድሜቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት ልጆቻቸው መድኃኒቱን እንዲወስዱ መፍቀድ እንደሚገባቸው ማስተማር
- በመድኃኒት ዕደላ ወቅት ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ለልማት ቡድን መሪዎችና ለመምህራን ኦረንቴሽን መስጠት

## 3.3. የማሕበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ለሚስፈልጋቸው ትሮፒካል በሽታዎች ቅደመ መድኃኒት ስርጭት ዝግጅት ማድረግ

- የቀበሌውን ሕዝብ ቁጥር በፆታና በዕድሜ በመለየት ህክምናውን መውስድ የሚገባቸውን የህብረተሰብ ክፍል መለየት
- ለማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት የሚያስፈልጉትን ግብዓት ፍላጎት ማዘጋጀት/ማቀድ
- አስፈላጊው ግብዓት ማቅረብ እና የስርጭት ቦታ መድረሱን ማረጋገጥ
- ተገቢውን የጤና ትምህርት መስጠትና የማህበረሰብ ንቅናቄ መፍጠር
- የስርጭት ቡድንን ማዋቀር፣ ስልጠና መስጠት እና የተዋቀረውን ቡድን በየስራ ድርሻው መደልደል
- የመድኃኒት እደላው በዋነኛነት የሚካሄደው በልማት ቡድንና የ1ለ5 ትስስር መሪዎች አማካይነት ሲሆን ከአንድ የልማት ቡድን ሶስት በስራ አፈፃፀማቸው ጥሩ የሆኑ አዳዮችን ከሴቶች የልማት ቡድን ዉስጥ በህብረተሰቡ አማካይነት እንዲመረጡ በማድረግ ቡድኑን ማዋቀር
- ለህብረተሰቡ ስለማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ገለጻ በማድረግ የመድኃኒት እደላ የሚካሄድበት ቀንና ቦታ በጋራ መወሰን
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙትን ተማሪዎች ሙሉ ስም ዝርዝር፣እድሜና ጾታ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ መመዝገብ፡፡
- በተማሪዎች ቁጥር መሰረት የሚያስፈልገውን የመድኃኒት መጠን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶች ፍላጎትን ማስላትና በመጠየቂያ ፎርሙ አማካይነት ጤና ጣቢያውን መጠየቅ፣ መረከብ እና ወደ ጤና ኬላው ማስመጣት

## 3.4. ትራኮማ (የአይን ማዝ) መከላከልና ማጥፋት

**ስለትራኮማ በሽታ ግንዛቤ ማስጨበጫ የጤና ትምህርት መስጠት**

- ማህበረሰቡ በየእለቱ ፊቱን እንዲታጠብ በማስተማር የበሽታውን አምጭ ህዋስ ከሰው ወደ ሰው እንዳይተላለፍ መከላከል
- የመኖሪያ አካባቢን ንፅህና፣ ውሀና የመጸዳጃ ቤት አገልግሎትን በማሻሻል ለዝንብ የማይመች ንጹህ አካባቢን መፍጠር

**የትራኮማ መንስኤ፣የሚተላለፍባቸው መንገዶች እና ምልክቶች**

**የትራኮማ መንስኤ**

- ዓይነ ስውርነትን የሚያስከትለው የትራኮማ በሽታ በዓይን በማይታይ ህዋስ/ባክቴሪያ የሚመጣ ነው፡፡

**መተላለፊያ መንገዶች**

- የሚተላለፈው የበሽታውን ሕዋስ ወይም ጀርም በተሸከሙ ዝንቦች አማካይነት ነው፡፡ እንዲሁም የታመመ ሰው የተጠቀመበትን ጨርቅና የታማሚውን እጅ ነክተን ሳንታጠብ ዓይናችንን ስንነካ የትራኮማ በሽታ ይከሰታል፡፡

**ምልክቶች**

- የዓይን መቅላት፣መሞጭሞጭ፣እምባ መውረድ፣ብርሀን መፍራት
- የላይኛው የዓይን ቆብ የውስጠኛው ክፍል መቆጣት አልፎም ማመርቀዝና ጠባሳ መፍጠር
- ህመሙ ሲባባስ የዓይን ሽፋሽፍት ወደውስጥ ተቀልብሶ ብርሀን አስተላላፊውን የዓይን ኳስ በመቦረሽና በመፈግፈግ ከፍተኛ የሆነ የዓይን ህመም ስሜት፣የዓይን ብሌን ወይም ኮርኒያ የሚባለውን የዓይን ክፍል ማበለዝ
- በመጨረሻም የእይታ መታወክ እና ዓይነ ስውርነትን ያስከትላል፡፡

**የትራኮማ በሽታ መከላከያ እና ህክምና**

- በትራኮማ(አይን ማዝ) ምክንያት የአይን ሽፋሽፍቶች የተቀለበሱባቸውና ወደ ውሰጥ የታጠፈባቸውን ታማሚዎች በመለየት የአይን ቆብ ቀዶ ህክምና እንዲደረግላቸው በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የህክምና ተቋም መላክ፡፡
- ተንቀሳቃሽ የአይን ቆብ ቀዶ ህክምበሚሰራበት ወቅት ለቡድኑ ስራ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

- አፍለኛ ትራኮማ የተገኘባቸው ታማሚዎች በመለየት ቴትራሳይክሊን የአይን ጠብታ በመጠቀም በጊዜ ማከምና የጀርሙን ስርጭት ማቀብ፡፡ ቴትራሳይክሊን ተጠቅመው ላልተሸላቸው ታማሚዎች የፀረ ተህዋሲያን መድኃኒት እንዲያገኙ ለተሻለ ሕክምና በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ መላክ

**የማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት መውስድ ላለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመድኃኒት እደላ ማከናወን**

- በመድኃኒት እደላ ወቅት መድሃኒት መውስድ የሌለባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መለየት
  - የእርግዝና ጊዜያቸው ከሶስት ወር በታች የሆኑ ነፍሰ ጡሮች፣
  - በሌላ በሽታ በጠና የታመመ ሰው፤

<u>**ማሳሰቢያ፡-**</u> ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት የህብረተሰብ አካላት ቴትራሳኪሊን የዓይን ቅባት መውሰድ ይችላሉ፤

**የመድኃኒት ፍላጎት መጠን መተንበይ**

| | |
|---|---|
| 1. ዚትሮማክስ (Zithromax) 250 mg ክኒን | ❖ አንድ ሰው የመድኃኒት ብክነትን ጨምሮ በአማካይ በአንድ የመድኃኒት ዕደላ ጊዜ 3 ዚትሮማኪስ ኪኒን ይወስዳል፡፡<br>❖ በቀበሌው ካለው አጠቃላይ ህዝብ ዚትሮማኪስ ክኒን መዋጥ ያላባቸው ከአጠቃላይ ህዝብ 84 በመቶ ነው<br>❖ አጠቃላይ የሚስፈልገውን የዚትሮማስ ኪኒን ለማግኘት የህዝብ ብዛት X 84% X 3 ነው፡፡<br>❖ ለምሳሌ በአንድ ቀበሌ 5000 ሰዎች ቢኖሩና የሚያስፈልገው ዚትሮማኪስ ክንነ ብዛት 5000 X 0. 84 X 3= 1,260,000 የዚትሮማስ ኪኒን ያስፈልጋል |
| 2. ዚትሮማክስ ፈሳሽ (Zithromax Syrup (7.5 ml) | ❖ በቀበሌው ካለው አጠቃላይ ህዝብ Syrup መውሰድ ያላባቸው ከአጠቃላይ ህዝብ 14 በመቶ ነው<br>❖ አጠቃላይ የሚስፈልገውን የSyrup መጠን ለማግኘት የህዝብ ብዛት X 0.14/4 ነው |
| 3. ቴትራሳይክሊን የዓይን ጠብታ ቲዩብ | ❖ በቀበሌው ካለው አጠቃላይ ህዝብ የዓይን ጠብታ መውሰድ ያላባቸው ከአጠቃላይ ህዝብ 2 በመቶ ነው<br>❖ አጠቃላይ የሚስፈልገውን የዓይን ጠብታ ቲዩብ ብዛት ለማግኘት የህዝብ ብዛት X 0.02/2 ነው |

**የመድኃኒት እደላ ማከናወን**

- ቁመት መለካት- እንደ አመጣጣቸው በማሰለፍ በተዘጋጀው የቁመት መለኪያ መሰረት መለካት
- መመዝገብ እና በቁመቱ ልክ መድኃኒቱን መስጠት
  - ከ6 ወር በታች ለሆኑ ህፃናት (በቀን 2 ጊዜ ለ6 ሳምንታት) የቴትራሳይክለን ቅባት መስጠት

- በተጨማሪም መድኃኒት ለመውሰድ ከመጡት ሰዎች ውስጥ የዓይን ቆባቸው የተቀለበሰባቸው እና ወደ ውስጥ የታጠፈባቸውን መለየትና የዓይን ቆብ ቀዶ ሕክምና ወደ ሚሰጥበት ጤና ተቋም መላክ

**መድኃኒቱ ሊፈጥር የሚችላቸው የጐንዮሽ ተጽእኖዎች (side effects) መለየት**

- ዚትሮማክስ ከሚጠቀሙ ሰዎች መካከል ከአስር አንዱ ላይ የማቅለሽለሽና የማስመለስ ስሜት፣ ተቅማጥ ወይም ሆድ ድርቀት ሊከሰት ይችላል፡፡
- መድኃኒቱን ለመውሰድ የተለዩት የማህበረሰብ አባላትም ስለመድኃኒቱ ተጽእኖዎች ዓይነትና ተጽእኖዎቹን ለማርገብ ሊወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ትምህርት መስጠት፡-
    - ተጠቃሚዎች መድኃኒቱን በባዶ ሆዳቸው መውሰድ የለባቸውም
    - ውሃ፣ ወተትና ሾርባ የመሳሰሉ ፈሳሾች መጠቀም ተጽእኖውን ለማርገብ ይረዳል፡፡
- ከላይ ከተገለጹት ቀላል የጐንዮሽ ተጽዕኖዎች የጠነከረ ተጽእኖ የተከሰተበት ሰው ካለም በአካባቢው በሚገኝ ጤና ጣቢያ ወይም  የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎች ወዲያው የሕክምና እርዳታ እንዲያገኝ ማድረግ
- በቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመት ችግር የለም፡፡ ነገር ግን መድኃኒቱ በታካሚው ላይ ያስከተለው ችግር ካለ ታካሚው ቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት መጠቀሙን እንዲያቆም ማሳወቅ ይገባል፡፡

**በትምህርት ቤቶች ዙሪያ በየጊዜው የንፁህ ፊት አሰሳ ማድረግ**

- በቀበሌው ውስጥ በሚገኙት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሌሎች ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች (school health program) ጋር በማቀናጀት የፊት ንጽህና አሰሳ ማድረግ

## 3.5. የኦንኮሰርኪያሲስ እና ተላላፊ የሆነው የዝሆኔ በሽታ መከላከልና ማጥፋት

### 3.5.1. ኦንኮሰርኪያስስን መከላከል መቆጣጠር

- ኦንኮሰርኪያሲሰ  ከሰዉ ወደ ሰዉ የሚተላለፈዉ በጥቁር ዝንብ አማካኝነት ሲሆን ይህ ጥቁር ዝንብ በበሽታዉ የተያዘ ሰዉ ከነከሰ በኂላ ወደ ጤነኛ ሰዉ ሄዶ ሲነክስ በሽታዉን ያስተላልፋል፡፡ ጥቁር ዝንብ በአብዛኛዉ የሚራባዉ ንፁህ ወራጅ ወንዝ ያለበት አካባቢ መሆኑን ግንዛቤ ማስጨበጫ ተገቢ ነው፡

**የበሽታው ምልክቶች ምንድን ናቸው?**

- ክፉኛ ማሳከክ (መፎከት)
- የቆዳ መቆጣት እና መቁሰል
- ሰዉነት ላይ የሚወጡ ጠጠር ያሉ እብጠቶች

- ❖ የእይታ ችግር ወይም ሙሉ ለሙሉ ማየት
- ❖ የጥቁር ዝንብ እጭ ባለበት ቦታ ፀረ ተባይ መድሃኒት መርጨት
- ❖ የበሽታው ምልክት የታየባቸው ሰዎች ለህክምና እና ለክትትል በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የህክምና ተቋም መላክ
- ❖ በዓመት ሁለት ጊዜ አይቨርሜክቲን የበሽታ መከላከያ መድሃኒት በመጠቀም የማህበረሰብ አቀፍ መድህኒት ስርጭት ማከናወን

### 3.5.2. ተላላፊ የሆነው ዝሆኔን መከላከልና መቆጣጠር

ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ በጥገኛ ትል አማካኝነት የሚመጣ እግርንና ሌሎች የሰዉነት ክፍሎችን የሚያሳብጥ በሽታ ነዉ፡፡ አብዛኛዉን ጊዜ ሰዎች በበሽታው የሚያዙት በልጅነት እድሜያቸዉ ቢሆንም የበሽታዉ ምልክቶች ጎልተው የሚታዩት ዘግየት ብለዉ ነዉ፡፡ በሽታው ከዓመታት ቆይታ በኃላ በወንድ ብልት አካባቢ ወይም በጡት ላይ እብጠት ያስከትላል፡፡ በወባ ትንኝና ሌሎች ተመሳሳይ ትንኞች አማካይነት በበሽታዉ ከተያዘ ሕመምተኛ ሰዉ በመንደፍ ወደ ጤነኛ ሰው ያስተላልፋሉ፡፡

**የበሽታው ምልክቶች ምንድን ናቸው?**

በዝሆኔ በሽታ የተያዘ ሰዉ ከሚታዩበት ምልክቶች ዋናዎቹ

- ❖ የእግር ማበጥ (ዝሆኔ)
- ❖ ማህደረ ቆለጥ ማበጥ/Hydrocoele/
- ❖ ጡት ማበጥ

- ❖ የበሽታው ምልክት የታየባቸው ሰዎች ለህክምና እና ለክትትል በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የህክምና ተቋም መላክ
- ❖ ማሕበረሰቡ በኬሚካል የተነከረ ፀረ-ወባ ትንኝ አጎበር (ዛንዚራ) እንዲጠቀም ማስገንዘብ እና ተግባራዊ መደረጉንም መከታተል
- ❖ በአመት አንድ ጊዜ የሚሰጠዉን መከላከያ መድሃኒት (አልቤንዳዞል እና አይቨርሜክቲን) መዉሰድ

❖ በበሽታዉ ለተያዙ የህብረተሰብ ክፍሎች ቤት ውስጥ ስለሚደረግ እንክብካቤ በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት

**የኦንኮሰርኪያሲስ እና ተላላፊ የሆነው የዝሆኔ በሽታ ለማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት የመድኃኒት ፍላጎት መጠን መተንበይ**

| ኪኒን/ መድኃኒት አይነት | የትንበያ ስሌት |
|---|---|
| ሜክቲዛን (Ivermectin) 3 ሚ.ግ ይህ አካባቢዉ ኦንኮሰርኪያሲስ ብቻ ካለ ይሰጣል | ❖ አንድ ሰው የመድኃኒት ብክነትን ጨምሮ በአንድ የዕዳላ ጊዜ በአማካይ 2.8 ሚክቲዛን (Ivermectin) ኪኒን ይወስዳል፡፡<br>❖ በቀበሌው ካለው አጠቃላይ ህዝብ ሚክቲዛን (Ivermectin) ኪኒን መዋጥ ያላባቸው ከአጠቃላይ ህዝብ 84 በመቶ ነው<br>❖ አጠቃላይ የሚስፈልገውን ሚክቲዛን (Ivermectin) ኪኒን ለማግኘት የህዝብ ብዛት X84%X 2.8<br>❖ ለምሳሌ በአንድ ቀበሌ 5000 ሰዎች ቢኖሩና የሚያስፈልገው **ሚክቲዛን (Ivermectin) ክኒን** ብዛት 5000 X 84% X 2.8= 11760 የአይቨርሜክቲን ኪኒን ያስፈልጋል |
| አልቤንዳዞል 400 ሚ.ግ በአካባቢዉ በተጨማሪ የዝሆኔ በሽታ ካለ ይሄ ከሜክቲዛን/ አይቫርሜኪቲን ጋር አንድ ላይ ይሰጣል | ❖ አንድ ሰው የመድኃኒት ብክነትን ጨምሮ 1.1 አልቤንዳዞል ኪኒን ይወስዳል፡፡<br>❖ በቀበሌው ካለው አጠቃላይ ህዝብ አልቤንዳዞል ኪኒን መዋጥ ያላባቸው ከአጠቃላይ ህዝብ 84 በመቶ ነው<br>❖ አጠቃላይ የሚስፈልገውን አልቤንዳዞል ኪኒን ለማግኘት የህዝብ ብዛት X84%X 1.1<br>❖ ለምሳሌ በአንድ ቀበሌ 5000 ሰዎች ቢኖሩና የሚያስፈልገው አልቤንዳዞል ኪኒን ብዛት 5000 X 84%X 1.1= 4620 የአልቤንዳዞል ኪኒን ብዛት ነው፡፡ |

**በመድኃኒት እደላ ወቅት አልቤንዳዞልና ሚክቲዛን (Ivermectin) መውሰድ የሌለባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች መለየት፡፡**

❖ ነፍሰ ጡሮች

❖ ከአንድ ሳምንት በታች የሆነ ጨቅላ ህፃን ያላቸዉና የሚያጠቡ እናቶች

❖ በማንኛውም ዓይነት በሽታ በጠና የታመሙ ሰዎች

❖ ከ90 ሳ.ሜ በታች ቁመት ወይንም ከ15 ኪ.ግ በታች ክብደት ያላቸዉ ወይም ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ናቸው።

**የማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት መውስድ ላለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የመድኃኒት እደላ ማከናወን**

❖ የመድኃኒት እደላ የሚካሄድበትን ሂደት እና ቦታ/ዎች መምረጥ፤ የመድኃኒት እደላ ለማከናወን ሁለት አማራጮች አሉ። አንደኛው ቤት ለቤት የሚካሄድ የመድኃኒት እደላ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጤና ኬላ ወይም በተመረጠ አማካይ ስፍራ ነው።

❖ ለቀበሌው/ጎጥ አማካይ በሆነ ቦታ ማድረግ ይቻላል

❖ ቁመት መለካት- እንደ አመጣጣቸው በማሰለፍ በተዘጋጀው የቁመት መለኪያ መሰረት መለካት

❖ መመዝገብ እና በቁመቱ ልክ መድሃኒቱን መስጠት

**የኦንኮሰርኪያሲስና ተላላፊ የሆነውን ዝሆኔን** በሽታ መካላከያ መድኃኒት የሚወስዱ ሰዎች የሚወስዱት ሚክቲዛን (Ivermectin)ና አልቤንዳዞል ኪኒን ቁጥር የሚወሰነው ቁመት በመለካት ነው። በዚህም መሰረት፡-

| የእንክብል አይነት | ቁመት | የእንክብል ብዛት |
|---|---|---|
| ሚክቲዛን (Ivermectin) 3 ሚግ | < 90 ሴ.ሜ | 0 |
| | ከ90- 119 ሴ.ሜ | 1 |
| | ከ120- 139 ሴ.ሜ | 2 |
| | ከ140- 159 ሴ.ሜ | 3 |
| | >159 ሴ.ሜ | 4 |
| አልቤንዳዞል 400 ሚግ | < 90 ሴ.ሜ | 0 |
| | > 90 ሴ.ሜ | 1 |

የኦንኮሰርኪያሲስና ተላላፊ የሆነውን ዝሆኔ መድኃኒቶች የሚወስዱ ሰዎች በጤና ኤክስቴንሽን ወይም በልማት ቡድን መሪዎች ፊት በአንድ ጊዜ መዋጥ አለበት። በተጨማሪም መድኃኒቱ በባዶ ሆድ መዋጥ የለበትም።

**የአይቨርሜክቲን መድኃኒት ጎንዮሽ ህመምና መፍትሄው**

❖ የኦንኮሰርኪያሲስ ወይም ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ ያለባቸው ሰዎች አይቨርሜክቲን ሲውጡ ራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ የቆዳ ሽፍታ፣ የአይን መቅላት፣ ማሳከክ፣ እብጠትና ተቅማጥ ሊከሰትባቸው ይችላል። ነገር ግን እነዚህ የጎንዮሽ ህመም መድኃኒቱ በትክክል እየሰራ መሆኑን የሚያመለክቱ ሲሆን ለከፋ ጉዳት አይዳርጉም።

- ይሁን እንጂ ይህ የጎንዮሽ ህመም ስሜት ቶሎ የማይቆም ከሆነ ከታየ ጤና ጣቢያ መላክ ያስፈልጋል፡፡

## 3.6. ተላላፊ ያልሆነው ዝሆኔ (ፖዶኮኒዮሲስ) መከላከልና ቁጥጥር

ይህ በሽታ ተላላፊ ያልሆነና እግር ለረጅም ዘመናት ያለ ጫማ ለቀይ ሸክላ አፈር ሲጋለጥ የሚከሰት በሽታ ነው፡፡

**ስለየበሽታው ምልክቶችና መከላከያ ዘዴዎች ግንዛቤ ማስጨበጥ**

**የበሽታው ምልክቶች**

- የመጀመሪያ ደረጃ ምልክቶች አብዛኛውን ጊዜ የእግርን የላይኛው ቆዳን ማሳከክ እና የታችኛውን እግርና መርገጫዎችን የማቃጠል ስሜት
- በእግር የላይኛው ቆዳ ላይ የተሰራጨ ወፍራም እብጠቶች መፈጠር
- ከተሰነጠቀ ቆዳ የሚወጣ መጥፎ ጠረን ያለው ፈሳሽ መኖር
- ወደኋላ ቆይቶ የሚፈጠሩት ጠጣር እብጠቶች ሁለት አይነት ሊሆኑ ይችላሉ ፣ ለስላሳ እና በፈሳሽ የተሞሉ ወይም ጠጣር እና በስሮች የተያያዙ ፤ አብዛኛውን ጊዜ ከጠጣር የቆዳ እብጠቶች ጋር የተያያዙ ናቸው
- አንዳንድ ጊዜ ህመምተኛው ትኩሳት ሊኖረው እንዲሁም እግሮቹን ሊያስነክሰውና ሊያመው ይችላል፡፡

**መከላከያ ዘዴዎች**

- ለህመም በሚያጋልጠው አፈር ላይ ጫማ ተጫምቶ መራመድ ወይም ቀጥተኛ ንክኪን መቀነስ
- በጎጆ ቤቶች ውስጥ መሬቱን የሚሸፍን ምንጣፍ ወይም መሰል ነገር ማንጠፍ
- በየቀኑ በንፁህ ውሃና በሳሙና እግርን መታጠብ

**ተላላፊ የሆነውና ያልሆነው ዝሆኔ በሽታ ታማሚዎችን መለየትና የህክምና አገልግሎት መስጠት**

የተላላፊ የሆነውና ያልሆነው ዝሆኔ ምርመራ የበሽታውን ምልክቶችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ተላላፊ የሆነውና ያልሆነው ዝሆኔ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚመሳሰል በምርመራ ወቅት መለየት ያስፈልጋል፡፡

በምርመራ ውቅት የታማሚው ታሪክ (የሚኖርበት ቦታ፣ ጫማ የመጠቀም ልምድ፣ )፣ አካላዊ ምርመራና እንደ አስፈላጊነቱም ከሌሎች በሽታዎች ለመለየት ሌሎች ምርመራዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ፡፡

**በተላላፊና ተላላፊ ያልሆነ ዝሆኔ ለተያዙ የህብረተሰብ ክፍሎች ቤት ውስጥ ስለሚደረግ እንክብካቤ በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት**

| |
|---|
| **ሀ) እግርንና ሌላም ያበጠ የሰዉነት ክፍልን ንጽህና መጠበቅ**<br>❖ እግርንም ሆነ ሌላ ያበጠ የሰዉነት ክፍልን ማጠብ መመረዝን/አንፌክሽንን ስለሚከላከል በንጽሁ ዉሃና ሳሙና በመጠቀም በንፁህ ጨርቅ በየጊዜው እንዲታጠቡ ማድረግ<br>❖ ያበጠዉ የሰዉነት ክፍል ለመድረስ የማይቻልበት ከሆነ የቅርብ ቤተሰብን/ዘመድ/ጓደኛን ድጋፍ መጠየቅና በደንብ ማፅዳት/ማጠብ የቆዳ እንክብካቤ ማድረግ -የቆዳ ድርቅትን ለመከላከል መደበኛ ፈሳሽ ቅባት ወይም ዘይት መጠቀም ይቻላል፡፡ በአቅራቢያው Whitfield ointment የሚገኝ ከሆነ ተመራጭ ነው፡፡ |
| **ለ) እግርንና ሌላም የታጠበዉን የሰዉነት ክፍል በጥንቃቄ ማድረቅ**<br>❖ እግርን ከታጠቡ በኂላ በጣቶች መካከልና ሌሎችም ከእብጠቱ ጋር ለተያያዙ ክፍሎች ትኩረት በመስጠት ንፁህ ጨርቅ በመጠቀም ማድረቅ፡፡<br>❖ በየቀኑ ንፁህ ካልሲ እና ጫማ ማድረግ- በእግራቸው እብጠት ያለባቸው ሰዎች በልካቸው ጫማ በማሰራት መጠቀም |
| **ሐ) ቀንም ሆነ ለሊት በመኝታ ወቅት በተቻለ መጠን እግርን ከፍ ባለ ሁኔታ ማኖር**<br>❖ በስራ ወይም በመኝታ ወቅት እግርን ከፍ አድርጎ ማኖር ከሰዉነት እብጠትን ሊቀንስ ስለሚረዳ በተቻለ መጠን እግርን ከፍ አድርጎ ማኖር |
| **መ) የሚለጠጥ ፋሻ መጠቀም**<br>❖ የፈሳሽ እብጠት ያለባቸው ህሙማን የታመመውን እግር ከጣት ጀምሮ እስከ ጉልበት ድረስ እግርን ከፍ አድርጎ በፋሻ መጠቅለል |
| **ሠ) በማንኛዉም ሰዓትና ስፍራ አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ**<br>❖ በቀን ዉስጥ በተደጋጋሚ የሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴ ያበጠዉን የእግር ክፍል ለማሻሻል ስለሚረዳ በማንኛዉም ስፍራና ጊዜ እንቅስቃሴ ማድረግ |
| **ረ) እብጠቶቹን ለማስወገድ ቀላል ቀዶ ጥገና ማድረግ** *(በተለይም ተላላፊ ላልሆነው ዝሆኔ)*<br>❖ ጠጣር እብጠት ያለባቸው ታማሚዎች ቀላል ቀዶ ጥገና ስለሚያስፈልጋቸው በአቅራቢያው ወደሚገኘው ወደ ጤና ተቋም መላክ ያስፈልጋል፡፡ |

**ሰ) አጣዳፊ የዝሆኔ ህመም  ሲሰማ ሊወሰዱ የሚገባቸዉ እርምጃዎች**

አጣዳፊ የሆነ የህመም ስሜት (ያበጠዉ ክፍልና ቆዳ ላይ ከፍተኛ ህመም፡ ትኩሳት፡ ራስ ምታት፡ ማንቀጥቀጥ፡ የማስመለስ ስሜት) በሚኖርበት ጊዜ

- ❖ እግርን በቀዝቃዛ ዉኃ ዉስጥ ማኖር
- ❖ በሐኪም የታዘዘ የህመም ማስታገሻ ኪኒን መዉሰድ
- ❖ በሐኪም የታዘዘ ቅባት በታመመዉ አካል ላይ በጥንቃቄ መቀባት
- ❖ ብዙ ዉኃ መጠጣት
- ❖ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ አለማድረግ

ይሁን እንጂ በማንኛዉም መልኩ ማድረግ የማይገቡ ነገሮች፡-

- ❖ በሙቅ ዉኃ መታጠብ
- ❖ ያበጠዉን ክፍል በመቧጠጥ ፈሳሽ ለማዉጣት ጥረት ማድረግ
- ❖ በሐኪም ያልታዘዘ ቅባት፣ አመድ ወይም ሌላ ነገር ማድረግ
- ❖ አጣዳፊ የሆነ የህመም ስሜት በሚኖርበት ጊዜ ህክምና መስጠት
- ❖ ያበጠዉ የሰውነት ክፍልና ቆዳ ላይ ከፍተኛ ህመም፣ ትኩሳት፣ራስ ምታት፣ማንቀጥቀጥ የማስመለስ ስሜት ሲኖር ህክምና መስጠት - አሞክሳሲሊን፣ፓራሲታሞል
- ❖ ቁስለት በሚኖርበት ጊዜ የቁስል እንክብካቤ ማድረግ (wound care)

**ሸ/ የስነልቦና ምክርና ድጋፍ**

- ❖ የዝሆኔ በሽታ በበሽታዉ በተጠቁ ሰዎች ላይ ከሚያሳድረዉ ህመምና የአካል ክፍሎች በማሳበጥ የአካል ቅርጽን ከማበላሸት ባሻገር በህመምተኞቹ ግለሰባዊና ማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚያስከትለዉ ተጽእኖና ቀዉስ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በመሆኑም በበሽታዉ ለተያዙ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊዉን የስነልቦና ምክርና ድጋፍ ማደረግ ያስፈልጋል( ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ፓኬጅ ውስጥ የአእምሮ ጤና ይመልከቱ)

## 3.7. የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች እና ለቢልሃርዚያ (ሽስቶሶሚያሲስ) በሽታ መከላከልና ቁጥጥር

### 3.7.1. የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች መከላከል እና መቆጣጠር

***መንስኤ፣ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች አስመልክቶ ግንዛቤ ማስጨበጥ***

- የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች በአፈር ውስጥ በሚገኙ ሶስት አይነት ጥገኛ ትላትሎችን ያጠቃልላል፤ እነሱም ወስፋት (አስካሪስ ሉምበርኮይድስ)፣ መንጠቆ ትል (አናክሎስቶማ ዶድናሊስ እና ኔካተር አሜሪካነስ) እና (ትርኩሪስ ትርኩራይ) ናቸው፡፡
- መንጠቆ የአንጀት ጥገኛ ትል በሽታ የሚከሰተው በዓይን በማይታይ የትሉ እጭ ቆዳን ሰርስሮ በሚገበበት ጊዜ ነው፡፡ ሌሎቹ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች ደግሞ እጅ ሳይታጠቡ በመብላት ፣በባዶ እግር በመሄድ፣ መጸዳጃ ቤት ባለመጠቀም፣ ንፁህ  የመጠጥ ዉሀ ባለመጠቀም፣ ምግብን አብስሎ ባለመብላት የሚከሰቱ ሲሆን በአጠቃላይ በአይነ ምድር በተበከለና የአካባቢ ንጽህና በጎደለው አካባቢ የሚከሰቱ የበሽታ አይነቶች ናቸው፡፡ በሽታዎቹ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚያጠቁ ሲሆን በተለይም ህጻናቶችና እናቶችን ለበሽታዎቹ በጣም ተጋላጭና ተጠቂ ናቸው፡፡

**የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች የበሽታ ምልክቶች፣**

- የሆድ ህመም ፣የምግብ ፍላጎት ማጣት፣የሆድ ማነፋትና መታወክ
- አቅም ማጣትና ዝለት
- የቀይ የደም ሴሎች እጥረት (የደም ማነስ) በተለይም የመንጠቆ ትል
- የዕድገት መገታት ፣መቀንጨር፣የአእምሮ ዝግመት
- የወስፋት ትል በአይና ምድረና በትውከት ውስጥ መውጣት አልፎ አልፎም በአፍንጫ ሊወጣ ይችላል
- በነፍሰጡር እናቶች ላይ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች የሚከተሉትን ሊያስከትሉ ይችላሉ
  - በእርግዝና ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የተለያዩ ሕመሞች
  - ክብደታቸው ከሚጠበቀው በታች የሆኑ ህጻናት መወለድ

**መከላከያ ዘዴዎች**

- በአንጀት ጥገኛ ትላትሎች የሚከሰት በሽታን በአጠቃላይ የአካባቢን ንጽህና በመጠበቅ፣ መጸዳጃ በመጠቀም፣ የግል ንጽህናን የምግብና የውሃ ንጽህናን በመጠበቅ መከላከል የሚቻል ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር የመከላካያ ዘዴዎችን መከተል አለብን፡፡
- ጫማ መጫማት
- ከመጸዳጃ ቤት መልስ በንፁህ ውኃ እጃችንን በአግባቡ መታጠብ

- ምግብ ከመመገባችን በፊት በንፁህ ውኃ እጃችንን በአግባቡ መታጠብ
- አትክልትንና ፍራፍሬን ከመመገባችን በፊት በንፁህ ውኃ በሚገባ ማጠብ
- በትምህርት ቤቶች የንጹሕ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል እና የመጸዳጃ ጉድጓድ በመቆፈር መጠቀም

**የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች ህክምና መስጠት**

**የማኅበረሰብ አቀፍ የበሽታ መከላከያ መድኃኒት ስርጭት ማከናወን**

- ለአንጀት ጥገኛ ትላትሎች የሚጠየቀው መድኃኒት ዓይነት ሜቤንዳዞል ሲሆን አንዳንድ ጊዜ አልቤንዳዞል የሚባለውን መድኃኒትንም መጠቀም ይቻላል፡፡
- በትምህርት ቤቶች የመድኃኒት ዕደላ ወቅት እያንዳንዱ ተማሪ የሚወስደው የመድኃኒት መጠን አንድ ኪኒን ብቻ ሲሆን የመድኃኒት እጥረት እንዳያጋጥም የሚጠየቀው የመድኃኒት ብዛት የተማሪዎች ቁጥር ሲባዛ በ1.1 ተደርጎ መሰላት አለበት፡፡ ለምሳሌ የተማሪዎች ቁጥር 1000 ቢሆን የሚጠየቀው የመድኃኒት መጠን 1,000 x 1.1 ይህም 1,100 የሜቤንዳዞል ወይም አልቤንዳዞል ኪኒን ይሆናል ማለት ነው፡፡

**ለሜቤንዳዞል ወይም አልቤንዳዞል ኪኒን የመድኃኒት ስርጭቱ የጊዜ ሠሌዳ እና አወሳሰድ**

የመድኃኒት ስርጭቱ በአመት ከአንድ ጊዜ በላይ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው በወረዳው እንደሚገኘው የበሽታ ስርጭት መጠን ሲሆን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

  - የበሽታው መጠን 50% እና ከዚያ በላይ ከሆነ በዓመት ሁለት ጊዜ
  - የበሽታው መጠን ከ20% — 49% ከሆነ በዓመት አንድ ጊዜ

- ሁሉም ህጻናት አንዳንድ ሜቤንዳዞል ወይም አልቤንዳዞል በማኘክ መድኃኒቱን ከሚሰጠው መምህር ወይም የጤና ባለሙያ ፊት መዋጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- ህጻናት መድኃኒቱን በሚወስዱበት ጊዜ ማስገደድ አስፈላጊ አይደለም፤ ምክንያቱም ለትንታ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- እንደበሽታው ስርጭት ሁኔታ ታይቶ የማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ከትምህርት ቤቶች በተጨማሪ በማሕበረሰብ ደረጃ ሊከናወን ይችላል፡፡

### 3.7.2. ለቢልሃርዚያ (ሽስቶሶሚያሲስ) በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር

**መንስኤ ፤መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት**

- ቢልሃርዝያ ሁለት የበሽታ አይነቶችን ያካትታል፤ እነሱም የአንጀት እና የሽንት ቧንቧ ቢልሃርዝያ በሽታ ይባላሉ፡፡ የአንጀት ቢልሃርዝያ ሽስቶሶሚያ ማንሱናይ እና የሽንት ቧንቧ ቢልሃርዝያ ደግሞ ሽስቶሶሚያ ሄማቶቢየም በሚባሉ ጥገኛ ትሎች የሚከሰቱ በሽታዎች ናቸው፡፡

❖ ሁለቱም የቢልሃርዝያ በሽታዎች ወደ ሰው የሚተላለፉበት መንገድ ተመሳሳይ ነው። መንገዱም አንድ ሰው የቀንድ አውጣ ጥገኛ ተህዋስ (ፓራሳይት ማለትም የሽስቶሶሚያሲስ እጭ) በተፈለፈለበት ውሃ ውስጥ ሲገባ ወይም ሲታጠብ በቢልሃርዚያ በሽታ ሊያዝ ይችላል ። በቀንድ አውጣው የተፈለፈለው ጥገኛ ተህዋስ (ፓራሳይት) ቆዳን በመብሳት ወደ ሰውነት ውስጥ ዘልቆ በመግባት በቀጥታ ወደ ሽንት ቱቦ ወይም ወደ አንጀት ውስጥ በመግባት እና በመራባት ጉዳት ያደርሳል ። ይህ ዑደት የሚቀጥለው በበሽታው የተያዘ ሰው በወንዝ አካባቢ ሲሸናና ሲፀዳዳ የሺስቶሶሚያሲስ እንቁላል ወደ ውሃው ስለሚገባ ነው።

**የቢልሃርዚያ በሽታ ምልክቶች ምንድን ናቸው**

በበሽታ የተያዙ ሰዎች መጀመሪያ ላይ ምንም አይነት ምልክት አያሳዩም ። ነገር ግን ካልታከሙ የሚከተሉት የበሽታ ምልክቶች ይከሠታሉ ፡-

❖ የሆድ ህመም ፣የሆድ መነፋት

❖ ደም የቀላቀለ ሽንት ወይም ዐይነ-ምድር ብሎም የደም ማነስ

❖ መቀንጨር፣የእድገት መገታት

❖ እንደ ጉበት ፣ ቆሽት ወይም የሽንት ፊኛ የመሳሰሉ ውስጣዊ የአካል ክፍል መጎዳትና ለሞትም መዳረግ

**መከላከያ መንገዶች**

❖ የንጹሕ ውሃ መገኛ በሆኑ ስፍራዎች አለመጸዳዳት እንዲሁም አለመሸናት

❖ የቆሻሻ አወጋገድን ዘዴ በማሻሻል ፤ የመፀዳጃ ጉድጓዶችን ቆፍሮ እንዲጠቀሙ ማድረግ

❖ የቀንድ አውጣ ያለበት ውሃን በኬሚካል ማከም፣

**የማኅበረሰብ አቀፍ (ትምህርት ቤት) መድኃኒት ስርጭት ማከናወን**

**ለቢልሃርዚያ (ለሽስቶሶሚሲስ) የሚጠየቀው መድኃኒት ዓይነት ፕራዚኳንታይል መጠን መተንበይና ለእደላው ቅድመ ዝግጅት ማድረግ**

❖ እያንዳንዱ ተማሪ የሚወስደው የመድኃኒት መጠን በቁመት የሚሰላ ሲሆን በትምህርት ቤት የሚገኙ ህጻናት ምንም ላይወሰዱ ወይም እስከ አምስት የፕራዚኳንቲል ኪኒኖችን ሊወስዱ

ይችላሉ፡፡የሚወስዱት መድኃኒት መጠን ከታች መድኃኒቱን መስጠት በሚለው ክፍል የሚገለጽ ሲሆን የሚያስፈልገውን የመድኃኒት ብዛት ለመጠየቅ ያክል ግን የተማሪዎች ቁጥር ሲባዛ 2.5 የሚለውን ስሌት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ከላይ እንደተገለጸው የተማሪዎች ቁጥር 1000 ቢሆን የሚጠየቀው የመድኃኒት መጠን 1,000 x 2.5 ይህም 2,500 የፕራዚኳንቲል ኪኒን ይሆናል ማለት ነው፡፡

- ❖ የተጠየቀው መድኃኒት የሚመጣበትን መንገድ ማመቻቸት፣ በየትምህርት ቤቶቹ በሚገኝ የተማሪ ቁጥር አንጻር የሚስፈልገውን የመድኃኒት መጠን እና ሌሎች ግብአቶች ማሰራጨት፡፡ በየትምህርት ቤቶቹ የሚሰራጨው የመድኃኒት መጠን ከላይ የተገለጸውን ስሌት የተከተለ መሆን አለበት፡፡
- ❖ ከመድኃኒት ስርጭቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ለትምህርት ቤትና ለተማሪዎች ማሳወቅ፣
- ❖ ተማሪዎች የወላጆች ይሁንታ አግኝተው እና ምግብ እና ውሃ ይዞ እንዲመጡ በማስገንዘብ መድኃኒቱን እንዲወስዱ መፍቀድ አለባቸው

**መድኃኒት መውሰድ የሚገባቸው ተማዎች መለየት**

- ❖ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኑ ዕድሜያቸው ከአምስት አመት በላይ የሆናቸው ልጆች መድኃኒቱን ይወስዳሉ፡፡ ትምህርት ቤት ያልገቡ ዕድሜያቸው ከአምስት አመት በላይ የሆኑ ህጻናትም በመድኃኒት ስርጭቱ ወቅት መድኃኒቱን እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

**መድኃኒት መውሰድ የማይገባቸው ተማሪዎች መለየት**

- ❖ በመድኃኒት እደላው ቀን የታመሙ ህጻናት
- ❖ እድሜያቸው ከአምስት አመት በታች ወይም ቁመታቸው ከ94 ሴ.ሜ. በታች የሆኑ ህፃናት
- ❖ ወላጆቻቸው መድኃኒቱን እንዲወስዱ ካልፈቀዱ
- ❖ የሚጥል በሽታ ያለባቸው ህፃናት

**በት/ቤት ለተማሪዎች የመድኃኒት እደላ ማከናወን**

- ❖ በትምህርት ቤት በሚካሄደው የትምህርት ቤት ተኮር የመድኃኒት እደላ ወቅት በመገኘት ለመምህራን እገዛ ማድረግ
- ❖ መምህራንና የተማሪዎች ተወካይ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት ሲያከናወኑ መመልከት እና አስፈላጊም ከሆነ እገዛ ማድረግ
- ❖ በገለጻው ወቅት የሚከተሉትን ጉዳዮች በግልጽ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
    - ○ መድኃኒቱን መውሰድ የሚገባቸውን ተማሪዎች፣
    - ○ መውሰድ የማይገባቸውን ተማሪዎች፣
    - ○ የመድኃኒቱን አወሳሰድ፣ የምዘገባ ሂደትን፣

- ○ መድሀኒቱን ከወሰዱ በኃላ የህመም ስሜት ቢከሰት ምን ማድረግ አለባቸው

- ❖ የመድኃኒት ስርጭቱ በጠዋት መካሄድ አለበት፡፡
- ❖ ተማሪዎች ምግብ እና ውሃ ይዞ መምጣት አለባቸው፡፡
- ❖ መድኃኒት ስርጭት ከሠዓት በኂላ ከሆነ ምሳቸውን ከበሉ በኂላ ይሆናል፡፡

**ሌሎች መድኃኒት መውሰድ የሚገባቸው ሰዎች መለየት**

- ❖ የበሽታው ስርጭት ከፍተኛ በሆነበት አካባቢ ዕድሜያቸው ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ የሆናቸው ሰዎች፣ እንዲሁም ነፍሰጡር እና የሚያጠቡ እናቶች እና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ቢኖሩ ለክልሉ ጤና ቢሮ ማሳወቅ ያስፈልጋል ፡፡

**የመድሐኒት እደላ ጊዜ**

- ❖ የበሽታው መጠን 50% እና ከዚያ በላይ ከሆነ በዓመት አንድ ጊዜ
- ❖ የበሽታው መጠን ከ10% — 49% ከሆነ በሁለት በዓመት አንድ ጊዜ
- ❖ የበሽታው መጠን ከ10% በታች ከሆነ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ቆይታቸው ጊዜ ሁለት ጊዜ እንዲያገኙ

**በመድኃኒት እደላ ወቅት የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጉዳቶችን መከታተል**

- ❖ የመድኃኒቶቹ አላስፈላጊ የጎንዮሽ ውጤቶች የሚያጋጥሙበት ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ቢከሰቱ እንኳን ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ እና መጠነኛ ናቸው፡፡
- ❖ መድኃኒት የወሰዱ ተማሪዎች አላስፈላጊ የጎንዮሽ ውጤት እንዳላጋጠማቸው ለሁለት ሰአት ያክል ክትትል ማድረግ፡፡
- ❖ የመድኃኒት የጎንዮሽ ጉዳቶችን ማከም እና እርዳታ ማድረግ፣
- ❖ በተደጋጋሚ የሚታዩት አላስፈላጊ የጎንዮሽ ውጤቶች እና መደረግ ያለባቸው እንክባካቤዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| አላስፈላጊ የጎንዮሽ ውጤት | መደረግ የሚገባው እንክብካቤ |
|---|---|
| መጠነኛ የሆድ ቁርጠት | ህጻናቱን መረጋጋትና ማበረታታት፣ ጸጥታ ባለበት ክፍል ለተወሰና ጊዜ እረፍት እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ውሃ መስጠት በተለይም ስኳር የተበጠበጠበት ቢሆን ይመረጣል |
| ማቅለሽለሽ | |
| ማስታወክ | |
| ተቅማጥ | |
| የድካም ስሜት | |

- ከአቅም በላይ የሆኑ የጎንዮሽ ጉዳቶች ከተከሰቱ በአቅረቢያው ወደሚገኝ ጤና ድርጅት መላክ እንዲሁም የጎንዮሽ ጉዳቶችን በተዘጋጀው ቅጽ መመዝገብ እና ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

<u>ማሳሰቢያ፡</u>

**የቢልሃርዚያ በሽታ ምልክት የታየባቸው ሰዎች በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ የህክምና ተቋም ሊላኩ ይገባል ፡፡**

## 3.8. ሊሽማኒያሲስ በሽታ መከላከልና ቁጥጥር

**የበሽታው መንስኤ ፣ መከላከያ ዘዴዎችና መተላለፊያ ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ**

- በሽታው የሚመጣው በአይን በማይታዩ በተለያዩ ሊሽማኒያ በሚባል ፕሮቶዞኣ ዝርያ ባላቸው ፕሮቶዞኣዎች አማካኝነት የሚከሰት መሆኑን፤ በሴቷ ፊሌቦቶማይን የአሸዋ ዝንብ (sand fly) ንክሻ አማካኝነት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ መሆኑን እና ንክሻውም ብዙ ጊዜ በምሽት ጊዜ የሚከሰት ሲሆን በቤት ዉስጥም ይሁን ከቤት ውጭ ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡
- በአብዛኛው የሚታየው የቆዳ ሌሽማኒያሲስ የተባለው በተለምዶ ቁንጭር የሚባለው ሲሆን ይህም በተነከሰው ቆዳ ማለትም በአፍንጫ ፣ አፍ ፣ እጅና እግሮች ላይ የሚታይ መሆኑን በሽታው ሲቆይም ጠባሳ፣ለማህበራዊ መገለል የሚያደርስ የአፍ ኅብረ-ህዋስ ሽፋንን ገጽታ የሚያበላሽ ቁስለትና የአካል ጉዳት እንደሚያስከትል ማስተማር
- ሌላው አይነት ሊሽማኒያሲስ ደግሞ በርካታ ውስጣዊ የአካል ክፍሎቻችንን የሚያጠቃ (በብዛት ጣፊያ፣ ጉበትን እና መቅኔን ያጠቃል) ሲሆን የሚያመጣው በሽታ የውስጥ አካል ሊሽማኒያሲስ ወይም ካላዘር እንደሚባል ግንዛቤ ማስጨበጥ፡፡
- በዚህ በሽታ የተጠቁ ሰዎች ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ትኩሳት፣ የክብደት መቀነስ፣የጉበትና የጣፊያ እብጠት፣የደም ማነስ ምልክት እንደሚታይባቸው፤ የዚህ አይነቱ ሊሽማኒያሲስ በሽታው እንደጀመረ ህክምና ካላገኙ ገዳይ እንደሆነ የጤና ትምህርት መስጠት

**መከላከያ ዘዴዎች**

- ሲተኙ ለረጅም ጊዜ በሚቆይ በኬሚካል የተነከረ አጎበር መጠቀም እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- በአግባቡ የሚከላከልን ልብስ መልበስ

- በቤት ውስጥ የሚረጭ ፀረ ተባይ መድኃኒት መርጨት
- የአሸዋ ዝንብ መራቢያ ቦታዎችን ማጽዳት

**በሌሽማኒያሲስ ተይዘዋል ተብሎ የሚጠረጠሩ ሰዎችን በሙሉ በቅርብ ወደ ሚገኘው የህክምና መስጫ ተቋም ሪፈራል መጻፍና ውጤቱን መከታተል**

- የበሽታው ምልክት የታየባቸውን ሰዎች ወዲያዉኑ ምርመራና ህክምና ወደሚሰጥበት አቅራቢያ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል በመላክ በሽታው እንዲረጋገጥ እና እንዲታከሙ ማድረግ
- በሽታው ወደ ሚገኝባቸው አካባቢዎች ሄደው የነበሩ ተጠርጣሪዎችን በመፈለግ እንደተገኙ የበሽታው ምልክት የሚታይባቸውን ወዲያዉኑ ምርመራና ህክምና ወደ ሚሰጥበት አቅራቢያ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል በመላክ በሽታው እንዲረጋገጥ እና እንዲታከሙ ማድረግ እና የበሽታው ምልክት ያልታየባቸውን ደግሞ ክትትል ማድረግ
- የበሽታውን መከሰት ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትና ለጤና ጣቢያ ሪፖርት ማድረግ፤እንዲሁም ቀሪ መረጃ በአግባቡ ማስቀመጥ

## 3.9. ጊኒዎርም በሽታ (ድራኩንኩልያሲስ) ጨርሶ ማጥፋት

**የጊኒዎርም በሽታ የሚከሰትበትና የሚተላለፍበት መንገዶች እና የበሽታው ምልክቶች ላይ ትምህርት መስጠት**

- የጊኒዎርም በሽታ ርዝማኔው ከ100 ሴ.ሜ በላይ በሆነ ገመድ መሠል ትል የሚከሠት አቅም የሚያሳጣ መሆኑን፤ ሰዎች በበሽታው የሚያዙት የጊኒ ትል ዕጭን የተሸከሙ የውሀ ቁንጫዎች (Cyclopes) ከሚገኙበት ኩሬ ወይም ማንኛውም የረጋ ውሃ የሚጠጡ ከሆነ እንደሆነ ለማሕበረሰቡ ትምህርት መስጠት ፡፡
- በበሽታው የተያዘ ሰው እስከ አንድ አመት ድረስ ምንም አይነት ምልክት ላያሳይ እንደሚችል ግንዛቤ ማስጨበጥ ፡፡
- ትሉ የበሽተኛውን ቆዳ በመብሳት ሊወጣ ጥቂት ቀናት ወይም ሳምንታት ሲቀረው ትኩሳት ፣ እብጠት እንዲሁም ትሉ ባለበት አካባቢ ህመም ሊሰማ እንደሚችል ማስተማር፤
- ከ90 በመቶ በላይ ትሉ የሚወጣው ከቅልጥም እና እግር አካባቢ እንደሆነ፤ ነገር ግን ትሉ ከሌላ የአካል ክፍል ላይም ሊወጣ እንደሚችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት ፡፡

**የጊኒዎርም በሽታ ህክምና እና መከላከል**


የጊኒዎርም በሽታን ለማከም መድኃኒትም ሆነ ክትባት የለም ፡፡ ስለዚህ ቀጣዩቹን ነጥቦች ማስተዋል ተገቢ ነው ፡፡

- እብጠት እና ቁስል ያለባቸው ሰዎች የሚጠጣ ውሃ ከሚቀዳበት ኩሬ ውስጥ እንዳይገቡ መከላከል
- ያልታከመ ውሃን ለመጠጥነት ከመጠቀም መታቀብ

❖ ያልታከመ ውሃን ለመጠጥነት የምንጠቀም ከሆነ በነጠላ ወይም የቧንቧ ማጥለያ ተጠቅሞ ማጥለል

❖ አቤት የሚባል የኬሚካል ዓይነት በኩሬ ውሃ ላይ መርጨት

**ትሉን የማውጣት ተግባርና ቁስሉን የማከም ሂደት/ዘዴ**




## 3.10. ድህረ ማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት

❖ ድህረ መድኃኒት ማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ዳሰሳ በማድረግ መድኃነቱን ያልወሰዱትን በመለየት እንዲወስዱ ማበረታታት እና እንዲወስዱ ማድረግ

❖ ቀሪ መድኃኒቶችን ቆጠራ በማድረግ ቀሪውን በመሰብሰብ ወደ ጤና ኬላ ብሎም ወደ ጤና ጣቢያ ተመላሽ ማድረግ፡፡ ነገር ግን በመድኃኒት እደላ ወቅት ላልነበሩ እና በተለያዩ ምክንያቶች ላልወሰዱ ሰዎች የሚሆን መድኃኒት ማስቀረት ያስፈልጋል፡፡

❖ በልማት ቡድን  እና ቀበሌ እንዲሁም በት/ቤት ደረጃ ግምገማ ማካሄድ

❖ የጎንዮሽ ጉዳት መከታተል እና ሪፖርት ማድረግ (የኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን  ቢጫ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ በመጠቀም)

❖ ከሁሉም  ልማት ቡድኖች እና ትምህርት ቤቶች የተሰበሰቡትን ሪፖርቶች ማጠናከር እና መተንተን እንዲሁም በቀጣይ ዕቅድ ወቅት በግብዓትነት መጠቀም፡፡

❖ ሪፖርት ማጠናከርና ለሚመለከተው አካል በወቅቱ መላክ (ከ1-2 ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ)

❖ ቀሪ ሪፖርትና መመዝገቢያውን በመሰበሰብ በትምህርት ቤትና በጤና ኬላ ማስቀመጥ

❖ የመድኃኒት ስርጭት ሽፋንን ማስላትና ለተገኘው ውጤት አስተዋጽኦ ያደረጉ መልካም ተሞክሮዎችንና ያጋጠሙ ችግሮችን ማካተት

## 3.11. የቬክተር ቁጥጥር ማድረግ

❖ የቬክተር መራቢያ ቦታዎችን መለየት

- የቬክተር ቁጥጥሩ ከሌሎች በሽታዎች የቬክተር ቁጥጥር ዘዴዎች ለምሳሌ፡ ወባ እና የመሳሰሉት ጋር አቀናጅቶ መምራት፣
    - ህብረተሰቡ የተለያዩ የበሽታውን መከላከያ መንገዶች እንዲተገብር ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ በጋራ ማቀድ፣ማስተባበር፣ማስፈጸም እና መከታተል
    - የቆሻሻ አወጋገድን ዘዴ በማሻሻል ፤ የመፀዳጃ ጉድጓዶችን ቆፍሮ በመጠቀም
    - የቢልሃርዚያ በሽታ አስተላላፊ የሆነውን ቀንድ አውጣ የተባለውን ቬክተር የያዙ የውሀ አካላት ማጽዳት፣ማፋሰስና መሙላት፣እንዶድን መጠቀም፣ ቦትና ጓንት መጠቀም፣ንፁህ ውሃ መጠቀም
    - የአሸዋ ዝንብ የሚኖሩበትን እና የሚራቡበትን ቦታ ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን መለየትና ማፅዳት
    - ህብረተሰቡን ለቬክተር ቁጥጥር በማነሳሳትና በማስተባበር የአሸዋ ዝንብ የሚኖሩበትን እና የሚራቡበትን ቦታ ጽዳት እንዲካሄድ ማድረግ
    - ለወባ በሽታ የሚታደለውን አጎበር በተገቢው መንገድ ሁልጊዜ መጠቀም
    - ለጊኒ ወርም አስተላለፊ ቬክተር መራቢያ የሚሆኑ ቦታዎችን መለየትና ማህበረሰቡን ማስተማር
    - ፀረ-ላርቫ የሆነውን የአቤት ኬሚካል ርጭት ማከናወን

## 4. አግልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

| ትራኮማ | ፎከት/ኦንኮ | ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ | የአንጀት ጥገኛ ትልትል፣ ብልሃርዚያ | ሌሽማኒያሲስ | ተላላፊ ያልሆነው ዝሆኔ | ጎኒ ዎርም ትል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br>ባትሪ፤ሉፕ፣ የእጅ ጓንት፤ ፀረ ጀርም ቅባት፤ የማስተማርያ ቁሳቁሶች፣ የቁመት መለኪያ ዘንግ (dosing stick)<br><u>መድኃኒቶች</u><br>ቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት፤ ዚትሮማክስ ክኒንና ሽሮፕ (ለመድሃኒትስርጭትወቅት) | <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br>የቁመት መለኪያ ዘንግ (dose pole)<br><u>Job aid</u><br>የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አጭር መመሪያ የመንደር መዝገብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ፖስተርና ቼክ ሊስት ፍሊፕ ቻርት<br><u>መድኃኒቶች</u><br>ሜክቲዛን 3 ሚ.ግ | <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br>የቁመት መለኪያ ዘንግ(dosing stick)<br><u>Job aid</u><br>የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አጭር መመሪያ የመንደር መዝገብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽፖስተርና ቼክ ሊስት ፍሊፕ ቻርት<br><u>መድኃኒቶች</u><br>አልቤንዳዞል 400 ሚ ግ፣ ሜክቲዛን 3 ሚ.ግ አንቲባዮቲክ፣ | <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br>የቁመትመለኪያዘንግ(dosing stick)<br><u>Job aid</u><br>የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አጭር መመሪያ መዝገብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ፖስተርና ቼክ ሊስት ፍሊፕ ቻርት<br><u>መድኃኒቶች</u><br>አልቤንዳዞል 400 ሚ ግ፣ | <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br><u>Job aid</u><br>የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አጭር መመሪያ መዝገብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ፖስተር<br><u>መድኃኒቶች</u> | <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br>ፋሻ፣ፀረ ባክቴሪያ ሳሙና<br><u>Job aid</u><br>የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አጭር መመሪያ መዝገብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ፖስተር<br><u>መድኃኒቶች</u><br>አሞክሳሲሊን፤ ፓራሲታሞል ፤Whitfield ointment | <u>የሕክምና ቁሳቁሶች</u><br><u>Job aid</u><br>የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች አጭር መመሪያ መዝገብ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ፖስተር<br><u>መድኃኒቶች</u> |

## 5. ጤና ኬላ ጤና ጣቢያ ትስስር

❖ የሪፈራል ትስስር (የዓይን ሽፋሽፍት የተቀለበሰባቸውን፣ጠጣር እብጠት ያለባቸው ዝሆኔ ታማሚዎች፣ ካላዛር ታማሚዎች፣ ሕክምና አገልግሎቱ ወደ ሚሰጥበት ጤና ጣቢያ መላክ). በትስስሩም፡

- መድኃኒት፤የሕክምና ቁሳቁሶች እና ሌሎች ግብዓት ማሟላት
- አቅም ግንባታ እና ድጋፋዊ ጉብኝት ማድረግ
- እቅድ ፤ሪፖርት ፤ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

## 6. የሚጠበቁ ውጤቶች

❖ ህብረተሰቡ አስፈላጊ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን ይፈጽማል፤ ተሳትፎውም ይጨምራል፣

❖ ትኩረት የሚሹ በሽታዎችን በመከላከልና በመቆጣጠር በህብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ህመም፣አካላዊ ጉዳት፣ ማህበራዊ ጫናና ሞት ይቀንሳል

❖ የማህበረሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ሽፋን ይጨምራል

❖ ተላላፊ የሆነውና ያልሆነው ዝሆኔ በሽታ ህክምናና ምክር ያገኙ ሰዎች ይጨምራል

❖ በየቀበሌው የህሙማን ፍለጋ አሰሳ ሥራ ይጠናከራል፤

❖ ለህክምና ወደ አቅራቢያው ጤና ጣቢያና ሆስፒታል ወዲያውኑ የሚላኩት ህሙማን ቁጥር ይጨምራል

## 7. ክትትልና ግምገማ

### 7.1. ክትትል

❖ በዚህ ፓኬጅ የተጠቀሱት ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መደበኛ የእቅድ አፈጻጸምን በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መፈጸሙን መከታተል (ለምሳሌ፤የማህበረሰብ አቀፍ መድሃኒት ስርጭት ወዘተ…)

❖ የእቅድ አፈጻጸሙ በዚህ ፓኬጅ የተቀመጡን ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ የተፈጸመ ከሆነ አጠናክሮ መቀጠል ነገር ግን አፈጻጸሙ ችግር ካለበት ሂደቱን ከእቅድ ጀምሮ መፈተሽና ማስተካከያ እያደረጉ መከታተል፤

❖ በሽታዎቹን በሚመለከት የተሰበሰቡ መረጃዎች ትኩረት የሚሹ በሽታዎችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ምን ያህል እያገዙ እንደሆን መከታተልና መከለስ፤

- በቅንጅት የሚሰሩ ተግባራት በባለድርሻ አካላት ምንያህል እየተፈጸሙ እንደሆን መከታተል

## 7.2. ግምገማ

- በፓኬጁ የተጠቀሱት ትኩረት የሚሹ የትሮፒካል በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እቅዶች ታቅደው በትክክል መፈጸማቸውን በጊዜ ገደብ አስቀምጦ መከታተል
- በተቀመጠላቸው የመመዘኛ የጊዜ ገደብና መለኪያዎች መሰረት የተፈጸሙ ተግባራትን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየት፤
- መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና በሁሉም አካባቢዎች እንዲፈጸም ማድረግ፣

## 7.3. ትኩረት የሚሹ በሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር ግምገማ መለኪያዎች

- ትኩረት የሚሹ በሽታዎችን መከላከልና ቀጥጥር ዙሪያ በግልም ሆነ በጋራ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት፣
- የህብረተሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ሽፋን
- የህብረተሰብ አቀፍ መድኃኒት ስርጭት ወቅት ጥቅም ላይ የዋለና የባከነ መድኃኒት ብዛት
- የስነ ልቦና ምክርና ድጋፍ ያገኙ ሰዎች ብዛት
- ትኩረት የሚሹ በሽታዎች (ተላላፊ የሆነውና ያልኮነው ዝሆኔ፣) የታከሙ የሕሙማን ብዛት፣
- በአሰሳ ወቅት የተገኙ ትኩረት የሚሹ በሽታዎች (ካላዛር፣ትራኮማ፣ተላላፊና ተላላፊ ልሆነው ዝሆኔ፣) ሕሙማን ብዛት፣
- ትኩረት የሚሹ በሽታዎች በተለይም ካላዛር፣ ብልሃርዚያ ምርመራ ወደ አቅራቢያው ጤና ድርጅት የተላኩ ሕሙማን ብዛት፤
- በካላዛር በሽታ የሞቱ ሰዎች ብዛት፤
- በቀበሌው ወረርሽኝ የሚከሰትባቸው ጊዜያት፣ ወረርሽኙም ቢከሰት የሚጠቁት መንደርና ሕዝብ ብዛት፣
- በቀበሌው የወባ ትንኝ መከላከያ ዛንዚራ /አጎበር/ የሚጠቀም ሕዝብ ብዛት፤

## 8. አባሪ

### አባሪ 1፡ ተላላፊ ያልሆነው ዝሆኔ (ፖዶኮኒዮሲስ) እና ተላላፊ የሆነው የዝሆኔ በሽታ (ሊምፌያቲክ ፊላሪሲስ) መለያ መንገዶች/ዘዴዎች

| ተላላፊ የሆነውን ዝሆኔ ተላላፊ ካልሆነው መለየት |
|---|
| ❖ ታማሚው የመጣበት/የሚኖርበት ቦታ - ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ በሽታ የሚከሰተው በቆላና ወይና ደጋ አካባቢዎች ነው፡፡<br>❖ እብጠቱ የጀመረበት ቦታ- ተላላፊ ያልሆነው ዝሆኔ (ፖዶኮኒዮሲስ) እብጠት ከታችኛው/ መርገጫ የእግር ክፍል በመጀመር ወደ ላይ የሚሰፋ ሲሆን ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ (ሊምፋቲክ ፍላሪያሲስ) እብጠት ደግም ከሙሃሂት ጀምሮ ወደ ታች እየወረደ ይመጣል፡፡<br>❖ ተላላፊ ያልሆነው ዝሆኔ (ፖዶኮኒዮሲስ) እብጠት ብዙውን ጊዜ በሁለቱም እግሮች ላይ የሚታይ ሲሆን ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ (ሊምፋቲክ ፍላሪያሲስ) እብጠት ግን ብዙውን ጊዜ በአንድ እግር ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ተላላፊ የሆነው ዝሆኔ (ሊምፋቲክ ፍላሪያሲስ) ከእግር ውጭ በብልትና በጡት አካባቢ እብጠትን ያስከትላል፡፡ |